# የታሪክ ቅሚያ ይሉታል ይህን ነው!

**ከሕድሪ መቐለ   02/27/14**

ታሪክ ያለፈውን ጊዜ እንደመስታወት ኮለል አድርጎ የሚያሳይ የሚያስተምር አውደ ትምህርት መሆኑ እገነዘባለሁ፡፡ ከበጎ ወይ ከሸንፈት ትምህርት ወስዶ ያ የሚተረክለት ትውልድ በጎ የነበሩት እሴቶች እንዲያጎለብታቸው ከነበሩት ስህተቶች ዳግም ስህተቱን እንዳይደግማቸው ለማድረግ ነው የሚጠቅመው፡፡ ካለበለዚያ ትውልድን ለማሳሳት ከሆነ ከሚሰጠው ጥቅም ጉዳቱ ነው የሚያመዝነው፡፡ ታሪክን ሊጠቅም ወይ ሊጎዳ አድርገው የሚቀርፁት ግን ተራኪያኑ ወይ የታሪክ ፀሓፊዎች ናቸው፡፡ የታሪክ ፀሓፊዎች ስነ ምግባር አንድ ወጥ አይደለም እንደየፈላጎታቸው ታሪኩን ይቃኙታል፡፡ ጥሩ ሊባሉ የሚችሉ የታሪክ ፀሓፊዎች እንዳሉ ሁሉ ታሪክ የሚያዛቡና የታሪክ ቀማኞች መኖራቸው እጅጉን ያስደንቀኛል፡፡ ይህ ክስተት በኢትዮጵያ ታሪክ ፀሓፊዎች ብስፋት ካሁን ቀደም ታይቷል ኣሁንም እየታየ ያለ ጉዳይ ነው፡፡

እንድኔ እምነት የታሪክ ፀሓፊዎች ካጥላቻ ከስሜታዊነት፣ ከውሸት፣ ከማጋነን፣ ነፃ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሚዛናዊ በእውነተኛ መረጃና ትክክለኛ ዋቢ ተጠቅም ድርጊቶችን በነበሩበት ደረጃ ተንትኖ ማቅረብ የሚችል መሆን ኣለባት፡፡

ስለ ትግራይ ህዝብ የሚፃፈው ብኣብዛኛው ሚዛናዊነት የጎደለውና ለአማራ ገዥ መደቦች በመደገፍ የትምክሕት አመለካከት የገዛው ታሪክ እንደነበር ከአፈወርቅ ገ/ዮሱስና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የተፃፉ መፅሓፍት ዋቢ ማድረግ ይቻላል፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ቢሆንም ተመሳሳይ ሸፍጥና የታሪክ ቅሚያ ሲጧጧፎ እንመለከታለን፡፡

በቸርቡ ነሀሴ 2005ዓ/ም በአለሙ ካሳ ረታ እና በሲሳይ መንግስቴ አዲሱ "የራያ ሕዝብና የማንነት ጥያቄ እና የማእከላዊ መንግስታት ምላሽ ከአፄ ዮሃንስ ፬ኛ እስከ ኢህአዴግ" የሚል መፅሓፍ ተፅፎ ለንባብ ብቅቷል፡፡ ብዙ አንባቢዎች እጅ እንደሚደርስ እገምታለሁ አንባቢዎችም የተለያየ ስሜት እንደሚፈጥርላችሁ መገመት አያዳግትም፡፡ መፅሓፍን ካነበብኩት በኃላ የሚከተሉትን ጥያቄዎችና ስሜቶች ፈጥሮብኛል፡፡ ብአጭሩ ያለኝን ሓሳብ ለመግለፅ እሞክራለሁ፡፡

የዚህ መፅሓፍ ደራሲዎች እንደተረዳሁት በተለይ ሲሳይ መንግስቴ ኣዲሱ የሚባለው የአብየታዊ ዲሞክራሲ ባለቤት የሆነው የቀድሞ ኢህዴን የዛሬ ብአዴን የሚባል ድርጅት አባል እንደነበር ተጠቅሷል፡፡ አሁን በአባልነቱ ይፅና አይፅና ግልፅ አይደለሁም፡፡

የመፅሃፉ አንኳር ጭብጥ “የራያ ህዝብ ማንነት ጥያቄ ሆኖ ራያ ራዮማ የተጓዘው የታሪክ ሂደት እንዳለ ተወስዶ አሁን ወደ አማራ ክልላዊ መስተዳድር ነው መካለል ያለበት የሚል ነው”፡፡ ድሮ በራያ የሚኖሩ ህዝቦች እንደነበሩ ብ15ኛውና በ16ኛው ክፍለ ዘመን ብኦሮም ህዝቦች መስፋፋት ምኽንያት ውህደት እንደተፈጠረ (Assimilatation) ከዛም በኃላ በዘበነ መሳፍንት ጊዘ በስርዓቶቹ ከፋፍለህ ግዛ ምኽንያት አንዴ ወደ ትግራይ አንዴ ወደ አማራ እየተካለለ አሁን የደረሰበት ደረጃ ስለ ደረሰ የራያ ትግርኛ ተናጋሪ የሆኑ ህዝቦች ትግሬዎች አይደሉም፡፡ ስለዚ ከአማርኛ ተናጋሪው የራያ ህዝቦች ጋር ነው መካለል ያለበት የሚል ክርክር አንስተዋል፡፡ ሆኖም ግን ለዚህ ክርክር በቂ ማስረጃ የላቸውም፡፡

የራያ ህዝብ ኦሮሞ ነው የሚሉን ከሆኑ ማንነቱ ኦሮሞ ሆኖ የራሱ የሆነ ልዩ ክልላዊ አስተዳደር ያስፈልገዋል ነው መሆን ያለበት ካልሆነ ደግሞ ኦሮሞነቱ በታሪኻዊ ሂደት በሌላ ማንነት ተቀይራል የሚባል ከሆነ ዳግሞ የ21ኛው ክፍል ዘመን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ነው መወሰድ ያለበት፡፡ ትግራይ ሆኖ ከሆነ ትግራይ አማራ ሆኖ ከሆነ ደግሞ አማራ ነው መሆን ያለበት፡፡

በታሪክ ሂደት የሃገሮችና የህዝቦች አካለል የቅኝ ገዥዎችና የነበሩት ገዥ መደቦች በቀየሱት መንገድ ነው ተካሎ የምናገኘው፡፡ ገዥ መደቦች በአንድ ቋንቋ ባህልና ሃይማኖት የህዝቦች ማንነት ነጥቀው ማንነቱ ሲቀይሩት ሲያዋህዱት ኑሮዋል፡፡ ለምሳሌ የአክሱም ስልጣነ የተሰፋፋበት ቦታ የመጀመሪያ ኑዋሪዎች የኩናማ ህዝቦች በታሪክ ይነገራል፡፡ ከጊዜ በኃላ ግን በትግራኛ ተናጋሪዎች ተገፍተዋል፡፡ የላሊበላና ከባቢው ህዝብ እስከ ዋግኸምራ አገው እንደነበሩ ታሪክ ይመስክራል የላስታ ህዝብ በጠቅላላ አሁን ብአማራዎች ተተክቷል፡፡ የየጁ ኦሮምዎችም ከሌላ ብሄር ህዝብ ጋር ተዋህደው በየጁ የኦሮሞ ማንነት ጥያቄ አሁን ማንሳት አይቻልም፡፡ እንድዚህ የመሳሰሉ ብዙ አብነቶች መጥቀስ ይችላል፡፡

በሃይማኖት ከታየም የመጀመሪያ የራያ ህዝቦች ክርስቲያኖች እንደነበሩ፡፡ በኃላ ግን ደራሲያኑ በመፅሓፋቸው እንደጠቁሱት ብአህመድ ግራኝ መሪነት በተካሄደ መስፋፋት እስልምና ሃይማኖት እንደተስፋፋ ቆይቶ ደግም ገሚሱ የራያ ህዝብ የክርስትና ሃይማኖት አማኝ እንደሆነ በሰፊው ፅፈዋል፡፡ በአሁኑ ጊዘ ሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች በመመካከር የሚኖርበት ከባቢ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ስለዚ አሁን ያለውን ሃቅ ነው መወሰድ ያለበት፡፡

የራያ ህዝብ የሚባለው ከዋጅራት ወሰን እስከ አለውሃያለው እንደሚያካልል የታወቀ ነው፡፡ ደራሲያኑ እንደሚሉት የራያ ህዝብ በትግራይ መጠቃለል ወይ መካለል የጀመረው ከአፄ ዮሃንስ ፬ኛ ሳይሆን የታሪክ ድርሳናት እንደሚያረጋግጡት ከ1772ዓ/ም ጀምሮ የትግራይ ገዥ የነበሩት ራስ ስሑል ሚካኤልን እሳቸውን የተኩት ራስ ወልደስላሰ ግዛታቸው ከአለውሃ እስከ ቀይ ባህር እንደነበር ይታወቃል፡፡ ዋና ከተማቸው ደግሞ በእምባ አርዓዶም ስር የምትገኘው ሕንጣሎ የምትባል ከተማ ነች፡፡ ቆየት ብለው የነገሱት

ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ከ1884ዓ/ም ዮሃንስ 4ኛ ከራያ ህዝብ የነበራቸው ግኑኝነት በደራሲያኑ እንደተገለፀው ነው፡፡ ኣብዛኛው ራያ በትግራይ ተካሎ ቀይቷል፡፡አፄ ምኒልክና አፄ ሃይለስላሰ ህዝብን በከፋፍላህ ግዛ ያደረሱት በደልና ግፍ ይታወቃል፡፡ የራያ ህዝብም እንደሌሎች ህዝቦች የዚህ ግፍ ቀማሽ በመሆኑ በየጊዜው ኣመፅ እያነሳ ይቃወምና ይታገል እንደነበር ይታወቃል፡፡ ትግራይ ን ለማዳከም ሲባል መሬቱን በተለያየ ጊዝ የተለያየ አካለል ይጠቀሙ ነበር፡፡ አንዴ ከአለውሃ ምላሽ ሌላ ጊዜ ራያ ቆቦ ወደ ወሎ ሲያካልሉት ቺይተዋል፡፡ ሰነድ ተንተርሰን እንወያይ ከተባለ አፄ ሃይለስላሴ በቁ 8/1942 ደምብ መሰረት ራያ ቆቦ፣ አላማጣ ዳዩ ዋጃ ቆቦ ቃሊም ጉራ ወርቄን ዞብልን ወደ ወሎ ጠቅላይ ግዛት እንዲካለሉ ተደረገ /ከቀዳማይ ወያነ በኃላ ማለት ነው/ ሆን ተብሎ ትግራይን ለማዳኽም የተሰራ ስራ እንደነበር ይታወቃል በዛን ጊዘ የነበረው ጥያቄ ከትግራይ ተቆርሶ ወደ ወሎ የሄደ መሬት ይመለስልን የሚል እንደነበር የፅሑፍ ሰነዶች ይመስክራሉ፡፡

ዘፈንም ወጥቶለት ነበር

“መሬትና እዩ ራያ ምስ ቆቦ

ወልቃይት ፀለምቲ መረብ ዝኽበቦ”

- ራያ ከቆቦ ወልቃይት ፀለምቲ ከመረብ ምላሽ መሬታችን ነው ይላል፡፡ ገዥ መደቦች በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲያቸው “ለአስተዳደር ይመቻል በሚል ፈሊጥ” ሲቆራርጡት ኑሯል
- ህዝቡም ብሂደት በግድም በውድም መወሃሃድ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ ይህ የማይካድ ታሪካዊ ሓቅ ነው
- የኢህኣዴግ መንግስት ገዥ መደቦችን ካሰወገደ በኃላ በመሬት ያለው ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት አድርጎ ማካለሉ ስህተት የለውም፡፡ ላስታ አገው ስለነበር ዛሬም አገው ነው አላለም ጎንደርና አካባቢው ቅማንት ነው አላለም ራያ ቆቦ ደግሞ ትግራይ ነው አላለም፡፡ ወሳኞቹ ደግሞ ደራሲያኑ እንደሚሉት ሳይሆን
- ኢህአዴግና ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት ነው፡፡ በፖለቲካ ስልጠን የበላይነት በመጠቀም በህወሓት አመራር ብቻ የተወሰነ አልነበረም እንደዚህ ያለ አስተሰሳሰብ ከትምክህተኞች ካልሆኑ ኣብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ካላቸው ግለሰቦች ሊፈለፍል ኣይችልም፡፡ ከተከዜ ወንዝ ባሻገር ከረዥም ዘመናት በትግራይ ስር ይተዳደሩ የነበሩ በአበርገሌና በቦራ ሰላዋ ሰር የነበሩ የአገው ብሄረሰብ ለምን ወደ ዋግ ኽምራ እንዲካለሉ ተደረገ ለአስተዳደር ምቹነት ቢሆን ማእነዚህ ኣካባቢዎ ለትግራይ ይመቻሉ፡፡ በነበር ብቻ መወሰን ኣይቻልም፡፡ ያለው

ተጨባጭ ሁኔታ መቅደም ስለ ኣለበት ነው የታሪክ ቁርኝት ካለው ህዝብ ጋር እንዲካለሉ የተደረገው፡፡

- የሚገርመው ነገር የራያ ዓዘቦ ህዝብ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ባልሆነ ቋንቋ ይዳኛል፣ ይተዳደራል እንዲማር ይገደደል ሲሉ ይከሳሉ፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ምንድነው ሲባሉ ግን የራያ ትግርኛ እንደሆነ መካድ ኣልቻሉም፡፡ ትግርኛ ቋንቋ እንደሌሎች ቋንቋዎች በየአከባቢው የራሱ የሆኑ የኣነጋገር ዘይቤ እንዳለው ይታወቃል የአማርኛ ቋንቋም የተለያየ ከባቢያዊ የአነጋገር ዘይቤ እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ የወሎና የጎንደር እንዲሁም የጎጃም አማርኛ አንድ ዓይነት እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ እንዲዚህ መሆኑ ደግም ቋንቋው ሃብታም መሆኑ ነው የሚያረጋግጠው፡፡ እንጂ የቋንቋ ልዩነት መኖሩን አየረጋግጥም፡፡ የራያ አዘቦ ትግርኛ ከሌላው ትግርኛ በምን ይለያል? ታድያ እነዚህ ፀሓፊዎች ቋንቋው የራያ ትግርኛ መሆኑ ካመኑ ለምንድነው ተገዶ በትግርኛ እንዲማር ይደረጋል የሚሉን፡፡ ኣይን ያወጣ ትልቅ ስሕተት ነው፡፡
- በዚህ መፅሓፍ በዛ ያሉ የተሳሰቱ መረጃዎች ተካተውበታል

1. የቀዳማይ ወያነ አጀማመር እድገቱንና የውድቀት ምኽንያቶቹ ተዛበቷል የታሪክ ቅሚያ በሰፋት የታየበት ክፍልም እዚህ ኣከባቢነው ፀሓፊዎቹ ለነሱ እንደሚመቻቸው አድርገው ፅፈውታል፡፡ እንቅስቃሴውን በሚመለከት ብዋናነት የተመከረበትና አመራር የተሰጠበት ማእኸል በወጀራትና በሕንጣሎ ማይ ደርሁ የሚባል ቦታ እንደነበር ሰነዶች ይመስክራሉ፡፡ ወያነ በራያ አልተጀመረም፡፡ በኋላ ግን ትስስር ፈጥሯል፡፡
2. በእንቅስቃሴው የተሳተፉት የራያ ወጀራት እንደርታ በራሰለዋ በራሰለዋ ክልተ አውላዕሎና ተምቤን ዓጋሜ ህዝቦች ናቸው የነበሩት፡፡ ከትግራይ በስተሰሜን የነበሩት ህዝቦችም እንደ ደኛዝማች ገብረሂይወት የመሰሉ ቀዳማይ ወያነን የተፋለሙ ባለባቶች አልነበሩም ባይባልም ህዝቡ ግን የወያኔ ደጋፊ ነው የነበረው፡፡ በሰነድ ማረጋገጥ ካሳፈለገ በጊዜው የትግራይ ጠቅላይ ግዛት ዋና ፀሓፊ የነበሩት በኩረ ወልደጊዮርግስ የተባሉ በ1937ዓ/ም ለሃገር ግዛት ሚኒስቴር የፃፉት ምስጢራዊ ሪፖርት የሚከተለውን ኣካትዋል፡፡ “የአድዋ ሕዝብ በጥቂቱ በክፍለ ሃገር ገዥ /ደጃዝማች ገብረሂወት መሸሻ/ በኩል ወደ መቀሌ ለጥበቃ ታዞ በግጭቱ ውስጥ ከዋለው በስተቀር በአገሩ ውስጥ ቀርቶ የነበረው በአገሩ ላይ ሁከት ለማንሳት አስቦ እንደነበር ያትታል፡፡ የደጃዝማች ገብረህይወት መሸሻ ወደ መቐለ ከዘመቱ በኋላ የአድዋን ህዝብ ለአመፅ አነሳስታችኋላ ተብለው የታሰሩ እነ ዳጃዝማች ሃይለስላሴ ገ/መድህን ደጃዝማች ኣብርሃ ኣስገዶምና ፊተውራሪ ገ/ኺዳንና ሌሎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዋቢ ቀዳማይ ወያነ በየማነ ገብረመስቀል”

3. ለቀዳማይ ወያነ ሽንፈት ምኽንያት በወያነ ኣመራር የሰሜን ትግራይ ባለቤቶች እጅ ስለነበረበት ነው የሚለው መረጃም የተሳሳተ ነው፡፡ ሆነ ተብሎ የተጠቀሰ ነው እንጂ ማረጋገጫ የለውም ለሽንፈቱ ምኽንያት የአመራር ጥበብ ማነስ ምኽንያትና የውጭ ሃይሎች እንደነ እንግሊዝ እጅ ስለ ነበረበት መሆኑ ኣይካድም የደቡባዊ ትግራይ ህዝቦች እንቅስቓሴ ሆኖ ስለ ተፈረጀ አልነበረም፡፡
4. በ1928ዓ/ም በጣልያን ወረራ ጊዘ የራያ ህዝቦች በገዥ መደቦች የተለያየ ግፍና በደል ቢደርስባቸውም አሰላለፋቸው ኣልፎ አልፎ ጥቂት በንዳዎች አልነበሩ ባይባልም ትክክልኛ አስላለፋቸው ከወገን ሃይል ጋር የው የነበረው፡፡ ለዚህም አስረጅ የሚሆንን በደጃዝማች አበራ ተድላ መሪነት በፅናት እየተዋጋ እንደዋለ ይታወቃል፡፡ የሃይለስላሰ ሰራዊት በፅናት እስከ መጨረሻው ስዓት ሳይወጋ ወደ ኃላ ለመሸሽ ሲያፈገፍግ ሲመለከት ግን ንጉስ እንዴት ለብቻችን ትቶን ይሸሻል በሚል እሳቤ ተበሳጭቶ ግን አፈሙዙን ወደሚሸሸው ሰራዊት መተኮሱ ከጠላት ጋር አብሮ ነበር አያስብልም፡፡ ድሮውንም ንጉሱ የትግራይ ህዝብ ጣልያንን አላስገባም በማለት ለ8 ወራት ብቻውን ሲፋለም አስቀድመው አልደረሱለትም፡፡ ከማይጨው ጦርነት በኃላግን ጠላት አዲስ አበባ ለመድረስ የወሰደበት ጊዘ ከአንድ ወር አይበልጥም ነበር፡፡ ለምን ብሎ የተመራመረና ጥናት ያካሄደ የታሪክ ምሁር ግን የለም፡፡ ሆኖም የራያ ህዝብ በመፅሓፍ እንደተጠቀሰው አሰላለፉ ከጠላት ጋር እንዳልነበር ይታወቃል
5. ከቀዳማይ ወያነ በፊትም ሆነ በኃላ በገዥ መደቦች በኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች በተለይ በትግራይ ህዝብ ይደርስ የነበረው ግፍና በደል ከልክ ያለፈ ከባድ ነበር፡፡ የትግራይን ህዝብ የራያን ህዝብ ጭምር ሆን ተብሎ ለማዳከም የተለያዩ እርምጃዎች ይወሰዱ ነበር፡፡ ልዩነት አልነበረውም የሰራዊት ቀለብ፣ ሕ/ሰቡ ዕዳ እንዲከፍል ብቁም ከበትም በማርትረዛ ብርና ብረት ገዝቶ እንዲከፍል ተጠይቋል፡፡ ሰብአዊ ክብሩም በተለያየ አኳኃን ተደፍሯል፡፡ የመፅሓፉ ደራሲያነ ግን በራያ ህዝብ የባሰ በሌላው በትግራይ አካባቢ ግን ሻል ያለ ነበር በማለት ቀለል አድርገው አቅርበውታል፡፡ ለዚህ ያቀረቡት ምኽንያት ደግሞ በቀዳማይ ወያነ የነበረው ተሳትፎ አናሳ በመሆኑ ነበር ለማለት ይዳዳቸዋል፡፡ ለመሆኑ ብዋናነት የተደራጉት ውጊያዎች በኩሓ አላጌና፣ ውቅሮ እምባ አርዓዶም እንደነበሩ ያወቁ ይመስለኛል፡፡ ታድያ ይህ እየታወቀ በህዝቡ ላይ የደረሰ ግፍና በደል ለምን ለማበላለጥ ተፈልገ የሚል ጥያቄ ይጭራል፡፡
6. የዚህ መፅሓፍ ደራስያን ስለ ቀደማይ ወያነ ሲፅፉ ምነው ወደ ወጀራትና እንደርታ ጎራ ብለው መረጃዎች አላሰባሰቡም የእንቅስቃሴው እምብርት ሳይነኩ ዳሩ ዳሩን ነው ለመዳሰስ የፈለጉት ለምን? የራያ አዘቦና የራያ ቆቦ ሰፍራዎች መጠርያ ብትግርኛ መሆኑ ለምን ይክዱታል፡፡

7. በመፅሓፍ የተጠቀሙባቸው በዘ ያሉ ዋቢ ያደረጉዋቸው ፀሓፊዎችና የሃገር ዳሳሾች እንዳሉ ሁነው አቀራረባቸው ግን ስነ ምግባር የጎደለው ነው፡፡ ለተነሱበት ዓላማ የማይደግፍ መሰሎ ሲታያቸው “የተጋነነ ነው” የሚል ነቀፌታ ያቀርባሉ፡፡ ዓላማቸውን የሚደግፍላቸው በተለይ ራያዎች ትግራይ አይደሉም የሚል ስሜት የሚሰጥ ከሆነ ግን ሰማይ ሲቆልሉት ይታያል፡፡ የሚገርምው ደግሞ የተጋነነው ሚዛን ለይተው አለማስቀመጣቸው ነው፡፡

8. እነዚህ ደራሲያን “የህወሓት አመራርን “የለማ መሬት ይቀማል” ብለው ሲከሱ ከሌሎቹ የትምክሕት ሓይሎችና ሊህቃን ምንልዮነት አሳቸው በሕገ መንግስቱ እምነት ካላቸው በህወሓት ላይ ያላቸው አመለካከት እንደዚህ ባልሆነ ነበር፡፡ ይህ የኣብዮታዊ ዲሞክራሲ ኣመለካከት መሰረት ያደረገ ሳይሆነ ትምክሕትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ሄዶ ሄዶ ሁሉም የራያ ህዝብ ወደ ኣማራ መካለል አለበት የሚል ድምዳሜ ጤነኛ ኣይደለም ዛሬ የራያ ህዝቦች ቁልፍ የሰላም ዲሞክራሲ ልማት የተሳታፊነትና የተጠቃሚነት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የራያ ህዝብ መልማት የኢትዮጵያ ህዝቦች መልማት ነው እንጂ ደረሲያኑ እንደሚሉት የትግራይ ወይ የኣማራ ህዝቦች ልማት ብቻ ኣይሆንም፡፡ የራያ ዓዘቦ ይሁን ራያ ቆቦ መልማት የሃገር ልማት ነው፡፡ ህዝብ ወደ ልማቱና ሰላሙ መልካም አስተዳደሩ ትኩረት እንዳያደርግ ተፈልጎ ነው ሌላ መልካም ያልሆነ ድግስ እየተደገሰለት ያለው፡፡ ሆኖም ግን ሰፊው የራያ ህዝብ የሚቀበለው አይደለም፡፡ የሚያዋጣው የሚያውቅ ህዝብ ስለሆነ የታሪክ ቅሚያ ለማንም አይበጅም፡፡ በሆነ ባልሆነ የትግራይን ህዝብ ለመከፋፈል አትሞክሩ፡፡ ያለፈው የትምክሕተኞች ሴራ ይበቃዋል፡፡ ራያ ራዩማ አንድላይ ወደ አማራ ይካለል የሚል አስተሳሰብ የህዝቡ ሳይሆን የጥቂት ያልሰለጡኑ ሊሀቃን አመለካከት ሆኖ በሂደት ይከሰማል የትግራይና የአማራ ህዝቦች የጋራ ጠላታቸው የነበረው ፋሽሽታዊ ደርግ አብረው እንደደመሰሱ አሁንም ፀረ ድህነት ትግላቸው ብተለመደው ሕብረታቸውና እንድነታቸው በጅመሩ የህዳሴ ጉዞ ሌላ አንፀባራቂ ድል እንደሚቀዳጁ አልጠራጠርም፡፡ በአንዳንደ አሉቧልታዎች ሽብረክ እንደማይል የህዝብ ጠላቶች ቢያውቁት ይሻላል የሚል እምነት ኣለኝ፡፡